# ሸሙጥ

## እንዳመቻችት የምትወጣ ነፃ ጋዜጣ

**ቁጥር** 2 **ሚያዝያ** 27 **ቀን** 1968 **ዓ.ም.**

*ይድረስ*

*ለልዑል ወንድሜ ለራስ መንገሻ ሥዩም። እንደምን ሰንብተሃል? እኛ ወገኖችህ በእግዚአብሄር ፈቃድ ደህ
ና ነን። ለልዑል ጌታዬ ለመርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ቀደም ብየ የፃፍኩላቸው መልእክት እንደ ደረሳቸውና ለአ
ንተ እንዳስተላለፉት ላኩብኝ። ከእንግዲህ ለአንተ ብፅፍ የሚያመች መሆኑን ገለፁልኝ። ትንሽ መጀመሪያ ላይ ግራ
የገባኝ ደብዳቤየን በጎንደር በኩል በአንድ ጎፈሬያም እንድልክና እርሱም ተስፋዬ ደበሳይ ለተባለው ካርቱም ለሚ
ኖር ተራማጅ ነኝ ባይ እንዲልክ መታዘዜ ነበር። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች እኛንም አልፎ አልፎ በሚሰድበው በስ
ውር ጋዜጣቸው በዴሞክራሲያ ዋና ተሳታፊና የኢትዮድያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲን ያቋቋሙት በመሆናቸው ነበር*

*ታዲያ እዚህ መሬት ይዞታ ሚኒስትር ያደረጉትን እኩይ እንዲቆጣጠር ያሾምነው አንድ የነቃ የተባ ዘመ
ዳችን ሲያጫውተኝ ነገሩ ሁሉ ገባኝ። ባለፈው ደብዳቤዬ እንዳሳሰብኩት ለካ እነሱም የጋራ ጠላታችንን አብረን እ
ንድነወጋ በበኩላቸው ተስማምተው ኖሯል። በሁሉም ነገር እንድንተባበር የኤርትራውም ግንባር ማዘዙን አጫውቶ
ኛል። አንዳንዴ ስድባቸው እኛንም ስለሚወርፈን ቅር ቢለኝም ካለእነ ኦስማን ሳላህ ሳቤ በስተቀር ማንም ስለማይቀ
ራቸው ራሴን አጥናንቼ እተባበራለሁ። በብዙም ነገር መወገኑ ጠቅሟል።*

*ስምምነቱ እኛ በየገጠሩ ያሁኑን ጉግ ማንጉግ አገዛዝ የሚቃወመውን የጨዋ ልጅ እንድናነሳሳ፣ ነጋዴውንም አ
ስተባብረን የተወቃው እህል ከተማ እንዳይገባ እንድናደርግ፣ የገበሬ ማህበሩንም እንድንበትን፣ ዘንድሮ እንዳይታረስ
እንድናግድ፣ በሹመቱም በኩል እነርሱም ሰዎቻቸውን ሲያስገቡ እኛም ጠንከር ብለን እንድንይዝና ትንሽም በገንዘ
ብ እንድነረዳ ነው። ገንዘቡ እንኳን እስከ ዛሬ ያነሳቸው አልመሰለኝም ነበር። ቀደም ብሎ እኔ እንደማውቀው ፅሁ
ፍ ለማባዣና ለማጓጓዣ፣ እንዲሁም ለሚያድሉ ስራ ፈቶች የሚከፈል፣ ለፖሊሱም እንዳያይ የሚረዳ በወር እስከ
10500 ዶላር/የአሜሪካኑን ማለቴ ነው የኛውማ መቅኖ አጥቷል/ ይላክላቸው ነበር። ታዲያ ወይም የውጭዎቹ ይቀየ
ሟቸው ወይም ደግሞ በትግሬና በባሌ ከኛ ሰዎች ጎን ላሰለፏቸው ሰዎች ይዋል ገና አልደረስኩበም እርዱን ማለት
አምጥተዋል። መሪዎቹም ማርያምና ሥላሴ አካባቢ የሚያካሂዱትን የእንግሊዝ ጠላ ቅምሻ የቀነሱ ይመስላል።*

*ታዲያ በችግራችን ላይ ችግር ተጨምሮ አንጣርያ ለአንጣርያ ቢደጋገፍ ተያዞ እንዘፍ እንዳይሆን ራሳቸውን ይ
ቻሉ ብለናል። ባይሆን ስድቧን እንዲቀንሱ ትንሽ እናግዛለን። ፈረንጆቹም እኛን ከመርዳት ይልቅ በአስተማሪውም
በአማካሪውም በኩል እነርሱን ሲረዱ ነው የምናየው። ቢሆንም የደርጉን ፋሽሽትነት ለማረጋገጥ መገፋፊያ ስለሚ
ሆን አይከፋንም። ይህንን ፋሽሽት ደርግ የሚያገለግለውንም ባንዳ ሁሉ /አዬ እዚህስ ላይ ጥሩ ብለውታል/ ለማጋለ
ጥ ይረዳል። ፋሽሽት፣ ባንዳ እያሉ መጮሃቸው ጥሩ ነው። ስም ይወጣ ከቤት ይከተል ጎረቤት እንዲሉ በዚህ አራ
ምዶ ይድፋውና ተራማጅ የሚባለው የሰፊው ህዝብ ድምፅ፣ ሬቮሉሽን፣ ወዝ /ነጫጭባው ሁሉ ወዛም ነኝ ሲል/፣
ነፃነት፣ የአብዮት ፋና፣ ታጋይ ኢትዮድያዊት እያለ እየሰየመ እየፃፈ ከሚያወናብደው ሁሉ ጋር አብረው አሲረው
እንዲነቅፉ እኛም እንድናስተጋባ ነው ሃሳቡ። ባላዋቂ ቤት እንግዳ ናኘበት እንዳይሆን የዚህን ተማርኩ የሚለውን ወ
ገን ጉዳይ እኛ ትተን እነርሱው ቢይዙት ነው የሚሻለው በሚል ነው።*

ትምህርት ቤቱ ሁሉ ባዶውን አፉን ከፍቷል። ይኸን መስታዎቱንማ ሲያንኮታኩቱት ወናው ማማሩ። ወደፊት አንበሳ የሚኖርበት ምድረ በዳ፣ ተኩላና ቀበሮ የሚተኛበት ጫካ፣ የዝንጀሮ መፈንጫ ውድማ እንደሚያደርጉት ሲታየኝ በደስታ ልቤ ይረካል። መንፈሴም በዚህ በመከራ ጊዜ ይታደሳል። እግዚአብሄር ከጎናችን እንደቆመ አምናለሁ። የርሱን ባሕረ ምስጢር ዋኝቶ የመረመረው ሁሉ ያጠፉናል ባልናቸው የተሰፋ ወይን ልምላሜ ሲያሳየን ለርሱ አምላካችን ክብር ምስጋና ይግባው ይላል። ተድላንም ይወርሳል።

በየገጠሩ ዘማች ተብሎ ሲተናኮለን የነበረውን ተማሪ ይሄው እዚሁ አዲስ አበባ ተጠራቀም ቢሉት ሰተት ብሎ መጣ። ማህበር እያለ ኩሊው ሁሉ እንዳያስቸግር የፋሽሽት ማህበር ይቅርብህ ብለውት ደህና አርፈን ነበር። አሁን እንኳን ማህበሩን ቢያቋቁም ግድ የለም። እነ በየነ ሰለሞን፣ እነ ማርቆስ ሃጎስ ተፈተዋል። እነሱም ባይችሉ ወገናቸው የሆኑ ወደር የሌላቸው ጠጉረ ረዣዥሞች ፋሽሽት ፋሽሽት እያልክ ጩህ ሲሉት መጮሁ አይቀርም።

በፅሁፍም በኩል ያ ድሮ በኛ መንግስት ጊዜ የደጃዝማች ወዳጅ የነበረ አሜሪካዊ ኢትዮጵያዊት አግብቶ ኖሮ አሁን በሷ በኩል የጨለማው ጊዜ እያለቀ እየደቀቀ መሄዱን ለማብሰር "ጎህ" የሚል ጋዜጣ አስጀምረናል። ከሬድዮውም፣ ከጋዜጣውም፣ ከቴሌቪዥኑም ደህና እያስተባበርን ነው። ከላይ የኛ ሰዎች አሉ። ይደግፏቸዋል። ከስር ሰለሞን ይዞት በነበረው ክፍል በመንግስት ገንዘብ ገበሬ እናስተምራለን እያሉ ደህና ይዘውልናል። እርሻው እንዳይታረስ ተደርጓል። ክብሩ ይስፋ።

በሴቶችም በኩል ደህና ይዘናል። ሴት ካልተደራጀች ብሎ አንድ ሰሞን ቢጨማለቅብን የምትሆን የምትሆነዋን፣ ዶሰኛ ምላሰኛዋን መርጠው ዴሞዎቹ አስገቡ። የሚያገኟቸውን ደርጎች ርስ በርሳቸው እያጋጩ ፈላጭ ቆራጭ ሆነው ቁጭ አሉ። ጥቂት ያስቸገሯቸውን ግፍንቶች ፈጠራና ልብወለድ ቢያስወሩባቸው በረገጉ። ጥቂቶች ሙጥኝ ቢሉ አባረሯቸው። ከዚያ ይኸውልህ ተንዘራፍጠው ይዘው "ከኛ ሌላ እስቲ ማነች ወንድ ሴት የምታደራጅ" ብለው ደህና አፍነው ይዘውልናል። ግዜህን አቃጥላለሁ እንጂ እነዚህ ልጆቻችን ራሳቸውን ሰውተው ሴቱ እንዲጠላቸውና ማህበር የሚሉ ነገር እርም እንዲል በዚህ ቀውጢና አጣዳፊ ጊዜ አንድ አመት ተኩል፣ የ13 ሚልዮን ሴት ግፊት ለመቋቋም ያደረጉትን ተጋድሎ በዘረዘርኩልህ ነበር። ፈጣሪ ይቁጠርላቸው።

እንዷን ታውቃት ይሆናል። የዳዊት አብዱ ልጅ ነች። የዚያ የልኡል ጌታየ ክርስትና ልጅ። ትንሽም ቢሆን እንደምንም የተጣቀሱት ነገር ደግ ነው። ታዲያ በኛ መንግስት ጊዜ አባቷ በአምባሳደርነት ካርቱም ሆኖ አንዴ በዚያ ሳልፍ አይቻት ነበር። ልጅ ነበረች። አሁን ደህና ይዛልናለች።

ሴት እኩል ነች ከተባለ ወዲህ አማርኛችን በተራክቦ ቋንቋ አዳዲስ ፈሊጥ ያሰማን ጀምሯል። ልጆቻችን "የሰፊዋን ሴት የመደብ ትግል እናስተባብራለን" ብለው ኮሚቴ አቋቋሙ ሲባል አገር ጉድ አለ። እኛ እንኳን ኮሙኒዝም ሴቱን የጋራ ያደርጋል ሲባል ቀደም ብለን ሰምተነው ስለነበረ ግር አላለንም። ትንሽ ግራ የገባን በዚህ በመጣ ጉዳይ ከዳር ሆነው ምኑን ከምን እንደሚያስተባብሩት አልከሰት ስላለን ነው። መቸም "እኛ እንትትን ሴቶች" ሲሉ ድፍረታቸውን አደንቃለሁ። ወታደሩም ነገሩን የጠላው አይመስልም። የቋንቋ አዋቂዎች ግን ተቃውሞ አሰምተዋል የሚሉ ሰምቻለሁ።

ወደ ቁምነገሩ እንመለስና እነዚህ ጎበዝ ልጆች ሊረዱ ይገባል። የጠሏቸው ዲሞ ወይም ዴሞ ይሏቸዋል። ከዴሞክራሲያ የተቀዳ መሆኑ ነው። ታዲያ እርሱም ቢሆን የሰደቧቸው መሰላቸው እንጂ ለጎበዝ የፈረሰ ስም ነው። የጅማን፣ የጎንደርን፣ የድሬዳዋን ግንብ ሁሉ በፅሁፋቸው ሲያጥለቀልቁት እናንተ ተመልሳችሁልን ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት የምታቋቁሙበት ቀን በየግድግዳው ተፅፎ ይታየኛል። ፖሊሱም ነገሩን ወዶታል። አስተማሪዎችም ያቺ የደሞዝ ነገር ስላለች አይጠሉም። በየጠቅላይ ግዛቱም ገዥዎች ውስጥ ውስጡን ይደግፋሉ። አሁን በዚያን ሰሞን እንኳን እዚህ ሃገረህይዎት / አንተም ትገዛው ነበር ታውቀዋለህ/ አንድ የኛ ሰው በኋላ የገደሉት ጀግና ከሁለት ዴሞዎች ጋር ሆኖ አገር በጠበጠ። ኦቶቡስ እንዲያቃጥሉ ተደርጎ ፖሊሱም በንቲ የተባለውም ገዥው በዝምታቸው ተባበሩ። ትንሽ የጎዳን ይኸ ቀን ወጣልኝ የሚለው ገበሬ ነው። ልጆቹን አስያዛቸው።

መቱና ጎሬም የኛ ሰዎች ዴሞ አስተማሪዎችና ዘማቾች ይዘው ጥቂት ስራ ፊት ገዝተው ይህን አገር የሚበጠብጠውን ሁሉ አጋለጡት። ለአገራችን ባዳ የሆነውን የቻይና መፅሃፍ የሚሸጥበትንም ሱቅ በታተኑት። ግን ምን ይሆና

ል። አምሳ ሰዎች እነ ባላምባራስ ገዳሙ ሳይቀሩ ስንት ትላልቅ አዛውንት አሰረብን። ልጃቸው ተካልኝም እንደ ቀላ
ል ሰው ተነሳ። የሎስ ያንሳቸውና። መቼ እነሱ ብቻ? ሰለሞን በኩረም ሳይቀር። እረ ስንቱን? ለጊዜው ጉድ ሆነናል።
ቢቻል በክፍሌ በኩል ወደናንተ እንዲመጡ ይደረግ። እዚህ "ብርሌ ከነቃ አይሆንም እቃ" ነው። አይረቡንም።
እሱንስ ባያነሱት አይደል? ብዙም ሰው ተያዘብን። አባታችንም የደረሰባቸውን ሰምተሃል። አሜሪካኖቹ እንኳን ሳይ
ቀሩ ቅር ተሰኝተዋል። ደግነቱ ምንም ቢሆን ከነርሱም ውስጥ ክርስቲያኖች የጨዋ ልጆች ስላሉን የዲቃሎቻቸው
ነገር ሳይነሳ ቀረ። ከታሰሩበትም እንዲያመልጡ ከሲቪሉም ከወታደሩም- አስተባብረን አምልጠው እርሳቸው ካሰሩ
ት ከጎፋ ሰፈር ገብርኤል ልከናቸው ነበር። ሳይቸግራቸው ወጥተው ጎጃም በረንዳ ሰአት እላፊ ተያዙብን።

ውድቀታችንን ስዘረዝር ነገሩ ሁሉ የከሸፈ እንዳይመስልህ። ብዙ የተወጠነ ነገር አለ። እኔም ራሴ በአለፈው ሰ
ሞን ለየካቲት መጀመሪያ ያቀድነው ሳይሰምር ቢቀር አዋቂ ዘንድ ሄጄ ነበር። ታዲያ ስለ ደርግ ብጠይቀው ብዙ አ
ጫወተኝ። ያስቃችሁ ብየ ነው እንጂ ነገሩ ቁም ነገር ኖሮት አይደለም። ከአለውማ ምን ተረፍን?

አዋቂው እንደሚለው ደርግ ግሱ ደረገ ነው። አንድ ሆነ፣ ተጋጠመ፣ በአንድ ታነፀ ማለት ነው። ነፋስ የማይገባ
ው ህብረትን ይገልጣል። የኛ መንግስት ኮሚቴ የሚለው ነው። ዛሬ ግን ለርእሰ ብሄር በአዋጅ ስለተሰጠ ቃሉ ተከበ
ረ። አስፈራ። ለደርግ ይዳርገኝ ካለ መሃላ ነው። ሲያማ ደርጎች ይላል። በጋልኛ ደርጊ ይለዋል። ታዲያ ቃሉ እን
ደሚገልጠው ሳይሆን ደርግ ጥርቃሞ እንጂ የተዋሃደ አይደለም። የፍካሬ ከዋክብት አዋቂዎች በጉጉት እንመስለዋለ
ን። እንደ ጉጉት ጭብጥ ያለ ነው። ክንፉን ግን አንዳንዴ ይዘረጋል። ክንፎቹን ልዘርጋ ያለ እንደሆን ሰፋፊ ግራ ክ
ንፍና ቀኝ ክንፍ ብዙም ንኡሳን አክናፍ ይታዩበታል። ሲከንፍ አንዴ ወደፊት አንዴ ወደኋላ አንዴ ወደታች አንዴ
ወደላይ ክፉኛ ድንብርብር ስለሚል ራድዮው አንዳንዴ በማስታወቂያ እያስመሰለ "በለው! ሽማግሌው ተደናበሩ እ
ንደ ልማዳቸው!" እያለ በአግብኦ ያሸሟጥጠዋል። እንደ ደርግ ያደናግርህ ከተባለ እንደ ክፉ እርግማን ይቆጠራል።
ከግራ ክንፉና ከቀኝ ክንፉ ላይ ኩስ የነካው ጭራ አለው። ጭራውን ሲጠየፈው "ከአብዮት በላይ ማንም የለም"
እያለ እያማተበ ያስከረክማል። ዝም ሲል ደግ አይደለም። ድፍን አገር ይደናገጣል።

ማርሽና ሸለላ ይወዳል። የፍየል ወጠጤ ቀለቡ ነው። ምሱን ያገኘ ለት ካልተደለቀ፣ ካልተሸለለ የበላው አይረ
ጋለትም። ቅዳሜ ቅዳሜ የኛን ሰፈር ያሸብራል። ላባው የኮርያ አረንጓዴ ነው። ሰረገላው ሮቨር ነው። ሌሎች የደ
ከሙበትን ለመውሰድ ሰብሳቢ እድል አለው። ጉረኛ ነው። መጀመሪያ ይደነግጣል። እየቆየ ግን ደፋርና ልበ ሙሉ
ይሆናል። በልጅነቱ ነጭ ክፍሉ ነው። እያደር ግን ይጠናወተዋል። ክፍሉ ገጠር ነው። ከተማ አይሆነውም። በዘንግ
ቆሞ መናገር አይችልም። ተቀምጦ ሲመክር ግን አዋቂ ነው። ሰላም ሲፈልግ ነገር ወዳለበት የመግባት እድል አለ
ው። በብዙ ነገር እድለኛ ነው። ነገር ግን እድሉን በገዛ ራሱ ያጠፋዋል። ወደኋላ ጊዜ ጥቅሙን አባራሪ እንዳይሆን
ያሰጋዋል። በየካቲት ስድስት ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ በውድቅት ለሊት መቅሰፍት ያስፈራዋል። ዴሞክራሲአይኤ
የተባለች የዛር ውላጅ ክፉኛ ትፈታተነዋለች። ነገር ግን ዴሞክራሲአይኤ ክፍሏ ቀንም ጨለማም ሳይሆን ጎህ ነውና
ትሸነፍለታለች። ተቸነፍኩ ብላ ትበርራለች። ትንሸ ቀይቶም ዴሞና ህብረት የሚባሉ ሁለት አካይስት ተባብረው
ይፃረሩታል። መድሃኒቱ የቢሮና የመሬት መዥገር በሰፊው ማሳደን ነው። መዥገሩን አስጨፍልቆ ከነጭ ተቀጥላ ጋ
ር ደባልቆ በአስራ አራት ወንድና በአንዲት አንስት አጋንንት ተከቦ በሱ ይታጠን።

ነጭ የተባለ ከግቢው አያስቀርብ። ትምህርተ ማርቆስና መልክአ ማኦ አፅፎ ይያዝ። አንድ ፅዋ የአብዮት ጠበ
ል በየቀኑ ከመጠጣት አይቆጠብ። የፍየል ወጠጤ እየሰበሰበ አይቀልብ። ወጠጤው ያድግና ትከሻው ይሰፋል፣ ልቡ
ያብጣል። ለጭሮ አዳሪው ይተውለት። ጭሮ ያወጣዋል። አርዶ ይጨርሰዋል። ቢላውን ብቻ ይስጠው። በቋራና በ
አምባሳጌ በባሌ የሚፈነጩትን አካይስት ቀንዳም ቀንዳሙን ጭዳ ያድርግ። ግልገል ግልገሉን ትምህርተ ቁስአካል
እያስደገመ ያስጠምቅ። በዘመነ ዩሃንስ ወንጌላዊ በሚያዝያ መጨረሻ ቅዳሜ ቀን ሲአይኤ የተባለ የዘመድ ጠላት በ
ፍየል ወጠጤና በዲሞ መድሃኒት ያደርግበታል። ዳር ስሜን አገር አይሆነውም። ከበረኸኛው ወዳጅ ያብጅ። አብረ
ው ደብረ ማርቆስ ወማኦ አንድነት ካልፀለዩ አይድኑም። አብረው ጠፊ ናቸው ይላሉ።" አለኝ።

እኔ እንኳን በኮከብ ቆጠራ እምብዛም ስለማላምን ነገሩን አነሳሁት እንጂ እውነት ነው ማለቴ አይደለም። ትን
ሽ የገረመኝ ከአብይ ፆም በፊት በፊት ያሰብናትን ነገር በማወቁ ነው። ወይም እርሱንም ገዝተውት ይሆናል። የድሮ

*አዋቂ ማርቆስንና ማኦን መች ይጠቅስ ነበር? ስለዚያ እርኩስ አጋንንትም ጠይቄው ነበር። “በጎህ መፅሄታችሁ 107*
*ጊዜ ስሙን አፅፈህ ያንን እሳት ጨምርና አመዱን ወላድ ሴት ፈልገህ በነጭ በግ ደም እየበጠበጠች ሰባት ጊዜ ታ*
*ስጎንጭህ። ስድስቱን ትፋው። ሰባተኛውን ግን የደመኛችሁ መጥፊያው ነውና እሱን ዋጠው።” ብሎኝ ነበር። ታዲ*
*ያ ይህ ሁሉ ተደርጎ በስንተኛው ቀን ነው ሰዎች አየነው ብለው አስደነገጡኝ። አልያዘም። በኋላ መልሼ ሳጠያይቅ*
*የአሜሪካኑ ሚስት ለካ ቁጥር ስታ 109 ጊዜ አፅፋው ኖሯል። በእኛ በኩል ትንሽ የዲሲፕሊን ጉድለት አለ።*

*“አድቮኬት” ጠበቃ ብላችሁ በፈረንጅ ቋንቋ ጋዜጣ መጀመራችሁን ከዚያ የመጣ ሰው አጫወተኝ። እኔ እንኳ*
*ን የጥብቅና የጥብቅና ሚዳቆ በዚህ ቅምዝምዝ በዚያ እንዳይሆንብን ወይ በኛው ቋንቋ እዚሁ ማስተባበሩ አይሻል*
*ም ነበር ወይ ይህስ ባይቻል እነዚያ እርኩሶች እንደሚያረጉት እዛው እያሳተማችሁ አትልኩልንም ነበር ወይ በሚል*
*ቅር ተሰኝቼ ነበር። ሰውየው እንደ ነገረኝ ከሆነ ለእኛ ቋንቋ እዚሁ ልጆቹ የሚያሳትሙት ይበቃል። እዚህ በፈረን*
*ጆቹ መውጣቱ ለዚያ መላወሻ የሚሆነውን ገንዘብ ለመሰብሰብ ያመቻል ሲለኝ ተፅናናሁ። “ጠበቃ” ብላችሁ በመሰ*
*የማችሁ ግን ሰው ግራ ተጋብቷል። ተራ ወንበዴ መንግስት ሆኖ ህግና ስርአት በጠፋበት ጊዜ በየትኛው ህግ ለመሟ*
*ገት ነው የሚል ጥርጣሬም ነበር።*

*ነገሩን ያብራራልን የሟቹ የደጃች ትርፌነህ ልጅ ነው። በአለፈው ሰሞን ዘመቻ ከሚሉት ኮብልሎ እዚሁ ከኛ*
*ጋር ነው ያለው። ታዲያ ጊዜው እናትና ልጅ የሚያጨካክን ሆነና የመጣ እለት እናቱ ወይዘሮ እልፍነሽ “ሶሻል ሶ*
*ሻል እያልክ አፍህን ስታሾል መሬቴን ያለፍርድ አስነጠከኝ፣ ህጋዊ ቤቴን ያለፍርድ አስወረስከኝ፣ ዛሬ ደግሞ ምን*
*ፈልገህብኝ መጣህ?” ብላ አያነሱ ድንጋይ አንስታ እናቱን ልትተረትረው ነበር። የዚያን እለት ሴት ልጃቸው በለጥሻ*
*ቸው ባሏ ከወታደር ጠርጥሯት እገላለሁ ቢል ጠፍታ እናቷ ቤት መጥታ ኖሮ ኡኡ ብላ ጎረቤት ደርሶ ገላገለ። ምን*
*አለፋህ ውካታ በውካታ ከሆንን በኋላ እኛም ደርሰን ነገር አብርደን ጠዋታ ጀመርን። ዘማች ኩራባቸው ሁሉንም*
*አስረዳን።*

*እናንተ “ጠበቃ” ብላችሁ መጀመራችሁን እሱም ነገረን። ልጆቹም ቀደም ሲሉ “ጠበቃህ እንጂ ነገረ ፈጅህ አ*
*ይደለሁም” በሚል ፅፈው እንደነበረ አወሳልን። በዚህም ያለ ስርአት ያለ ፍርድ ለደረሰብን በደል የምንፋረድበት*
*ቀን መቃረቡን አበሰረልን። የኛ ሰዎች ከልጆቹም ጋር ተነጋግረው በውስጥም በውጭም ህግ ሲመለስ ለእሰጥ አገባ*
*ው ዝግጅት ተጀምሯል አለን። አብዮታዊ ወጣት በተሰኘው ወረቀታቸው ላይ “ህጋዊ ቤታችን ተነጠቀ” በሚል አዘ*
*ናግተው ጣል ማድረጋቸውን፣ ላብ አደር በተሰኘልን ጋዜጣም “መሬት ተነጠቀ” ብለው ዳር ዳር ማለት መጀመራቸ*
*ውን አስረዳን። ይህንን ሁሉ የሚያስተባብርልን ተወዳጅ ጋዜጣችንን ልጁ ሁሉ “ዴሞክራሲያየ” እያለ እንደሚጠራ*
*ው ጠላቶቹ ግን “ዴሞክራሲአይኤ” ብለው እንደሚጠሩት ነገረን። ልዩነቱ ግን አልተከሰተልንም። ምሁራን ናቸውና*
*ያውቁታል ብለን ዝም አልን። በእናንተም በኩል ያሉት ልጆቻችን በአሜሪካን አገር ተሰብስበው አምና በነሃሴ ወር*
*ይህ አህዛብ ጉግ ማንጉግ ወንበዴ ያለፍርድ ህጋዊ ቤታችንንና መሬታችንን ነጠቀን እንጂ በኮሙኒስትም ቢሆን ባይ*
*ሆን ሃይማኖት ይከለከላል እንጂ መሬት አይነጠቅም፣ በእርስትነት መመለስ አለበት ብለው ከአዋቂዎች እየጠቃቀሱ*
*መወሰናቸውን ነገረን። ወላድ በድባብ ትሂድ እንጂ ህጋዊ ቤታችንና መሬታችን እንደተነጠቁ አይቀርም! ይህ እንግ*
*ዲህ በአዋቂዎችም ያልተደገፈ እውነተኛው ኮሙኒስት ሳይሆን ወንበዴ ጉግ ማንጉግ መሆኑ ነው ማለት ነው። ድሮ*
*ስ ቢሆን ከኛ ወዲያ ኮሙኒስት። አንተም የምታውቀው ነው። አሽከሩን ትቶ የሚበላ ማን ነበር? ልጆቻችን ከመፅሃ*
*ፍ እየጠቃቀሱ ይህንን ሁሉ እያስረዱ ነው።*

*ባለፈው ሰሞን እንኳን ከመተንፈስ አቅም መተንፈሻ ሲያሳጣን “ዴሞክራሲ በገደብ” እያለ ባንዳው ሁሉ ሲደነ*
*ፋ ኩራባቸው ስሙን ሃማቾ ማሆጋኖ በሚል ለውጦ ቀጥ አድርጎ እንደተከራከረልን ይህንን ተራማጅ ነኝ የሚል ፎ*
*ቃቃ የድሃ ልጅ ሁሉ መልሶ አፉን እንደገደበልን አበሰረልን።*

*ይሄኔማ ተወኝ። መልሰን ወይዘሮ እልፍነሽን ማባበሉ ባሰን። “ወይኔ ልጄን! አሁንም ኮሙኒስት መስሎኝ ገድየ*
*ው ነበር! እውነትም ጠበቃ! የምን ነገረ ፈጅ! ወይኔ! የህጋዊ ቤቴ ጠበቃየን ገድየ ነበር። ወይኔ በሞትኩት.....” እያሉ*
*እየየ ሆነ። ልጁም አዋቂውም ሃይ ሃይ ብሎ ነገሩ በረደና አንድም ሶስትም የሆኑትን የስላሴዎችን ምስጢር እያደነ*
*ቅን ጉድ አልን። ታዲያ ፊታውራሪ ቶሎሳም ከጭሰኞቻቸው መግባባት እያቃታቸው ተቸግረው እኛው ጋር ነበሩና ‘*

'ታዲያ ልጄ እናንተም ለህጋዊ ቤታችን ጠበቃ ስትሉ፣ እኛም ለህጋዊ ቤታችን ጠበቃ ስንል ይኸ ምናምንቴው አይ
ጠረጥርም?" በሚል ጣል አደረጉ። ኩራባቸውም "አወን ሊመስል ይችላል። እኛ ግን ከግራ ነን።" ብሎ ትንሽ ግራ
አጋባን። ነገሩ ሳይብራራ አሽከር ገብቶ "ማርታ ዋለልኝ ነኝ የምትል ልጅ መኪና ይዛ ቆማለች" ቢለው እየከነፈ
ወጣ።

ለአሁን ግን ጎራው የጭንቅ የመከራ ሆኗል። ደርጉን አስጨንቀን ይዘናል። በሸዋ ከበደ ብዙነሽ፣ ደጃዝማች
አስራት የሌሊት ቁር የመአልት ሃሩር ተቀብለው በአንድ ፊት ይዘዋል። ዴሞዎች ናዝሬትን፣ ደብረ ዘይትን፣ አቃቂ
ን፣ መቂን ለማዘረፍ ስራ ፈቱን ያነሳሳሉ። አዲስ አበባም ለሚያዝያ 23 ደርጉ ያዘጋጀውን የሰራተኛ ቀን በደም ባህ
ር እንዲጥለቀለቅ እንዲያደርጉ ተነጋግረናል። ካልተጋደሉ ደመኛ መሆን አይቻልም። ነገሩ ቀላል ነው። ደመወዝ
እቀንሳለሁ ብሎ ስለሚቀባዥር ዋና ዋናዎቹ የአየር መንገዱ፣ የባንኮቹ፣ የኢንሹራንሶቹ መሪዎች ቅር ተሰኝተዋልና
ተነስተውበታል። ኤርትራ ትገንጠል የሚል ፅሁፍ ይዘው ከወጡ ወታደሩ ቢታዘዝም ባይታዘዝም መተኮሱ አይቀር
ም። ትንሽ ከደቆሱትም ይተኩሳል። ካልተሳካም እንተኩስበታለን። ያኔ ዝም ብሎ አያይም። ጥል ያለሽ በዳቦ የሚ
ል አናጣም።

ሰሞኑን ደሞ የተያዘው ውይይት የሚሉት ነው። ባንዳዎቹ ዴሞዎቹን ለማሸነፍ እንችላለን በሚል ፎክረው በጋ
ዜጣ ውስጥ እንከራከር ብለው አስፈቅደው አንድ ሰሞን እሰጥ አገባው ቀልጦ ነበር። የጦጣን ልጅ በዛፍ የፀጋን ል
ጅ በመፅሃፍ ማን ይችላል እንዲሉ እኔ አይሆንም ይቅር፣ ባንዳዎቹ አይቻሉም፣ ብቻቸውን ይለፍልፉ፣ ተው በኋላ
እንዋረዳለን ብየ መክሬ ነበር። አሁን ሲያዩት ተቀብለውኛል። እነሱ እንኳን አንዳንድ ጋዜጠኞችን ስለያዙ ይጠቅ
መናል ብለው ነበር። በነፃ መከራከር አልተቻለም ብለው ሊወጡ ተቆርጧል። ዞሮ ዞሮ ጉዳዩ የሚጎዳው ሁለቱም
ወገን የሚጠቅሰው ያንኑ የጉግማንጉግ መፅሃፍ ስለሆነ አንዱ ሲናገር ያፈዝ አንዱ ሲናገር ያደነዝዝ እየሆነ ህዝቡን
መመረዝ ነው በሚል ነው። ዴሞክራሲ የሚሉት እውነት ያለገደብ ቢሆንማ የኛን የኛን እየጠቀስን እናሳየው ነበር።
የምግባራትን ሸቶ እያሸተትን በሃይማኖት የህዝቡን ልብ እንሰብቀው ነበር።

አሁን ደግሞ በየመስሪያ ቤታችሁ ተወያዩ ብለዋል። እርግጥ ደርጉን ለማማት ከተቻለ ይጠቅመን ነበር። ግን
አርእስት እየወሰኑ ወደዚያው ወደ ኮሙኒዝም ማስተማር እንዳያዘነብል ስለሚያስፈራ ዴሞዎቹ በጠነከሩበት መስሪ
ያ ቤቶች ወይም ለአለመወያየት፣ ገፍቶ ሲመጣም ሌላ አርእስት እየተዘጋጀ እንዲነጋገሩ እየተሞከረ ነው። ሰው ሁ
ሉ ተሰባስቦ ደርግ ይውደም ሲል ለአመሉ ይቅር ይል የለ? ለኛ የሚጠቅመን ውይይት ሆድ ባዶ ይጠላልና የመከራ
እንጀራን የሚመገበው ይሄ ስራ ፈቱ በየሰፈሩ በየእድሩ ስለችግሩ ሲወያይ፣ ነጋዴውም፣ ካህናቱም፣ የቢሮ ፀሃፊው
ም ስለ ደመወዝ መቀነስ፣ ስለ ታክሱ መብዛት፣ ስለ ሃይማኖት መደፈር ሲወያይ ነው። ወደዚያው እንወስደዋለን።
ግድ የለም።

ስለሆነም ውድ ልኡል ወንድሜ እናንተም ተዘጋጁ። ብልህ የአመቱን ሞኝ የእለቱን ነውና የአሁኑን ዴሞዎቹ ይ
ዘውልናል። እኛ የወደፊቱን እናዘጋጅ። ወደ ሎንዶን በቅርቡ የላክነው መኮንን እንደጀመረላችሁ ሁሉ አምባሳደሮ
ቹን አስተባብሩ። አሜሪካኖቹም አሁን መለስተኛ ብሎ እቅዱን አውጅዋልና የቀረቻቸውን ተስፋ እንዲቆርጡና በ
ጦር ሃይሉ ውስጥ ያሏቸውን መኮንኖች እንዲያንቀሳቅሱ ገፋፏቸው። እስከ መቼ አድብተው ሊቆዩ? ኦስማን ሳላህ
ሳቤም አረቦቹ ለእነርሱ ብቻ ሳይሆን ለእኛም ይበልጥ እንዲረዱ እንዲገፋፉ ይደረግ። አስመራ እንደወደቀች የጥን
ት መንበረ መንግስቱን ጎንደርንና የደቡቧን መዲና ጅማን እንድንይዝ ዝግጅቱ ይቀጥል። ሱማሌም ጋር ንግግር መ
ጀመር ነው። እስከ ጅጅጋ ቢይዙ ይበቃቸዋል። ጂቡቲንም ቃል መግባት ነው። እርግጥ ኋላ ይቸግረናል። ግን ወተ
ቷንም አልለቅ ጥጃየም አይከሳ አይሆንም። አሜሪካና ሎንዶን ያሉት የዴሞ ሰዎች በስድብ ብቻ መወሰናቸው አልገ
ባኝም። የኤርትራን ተማሪዎች ጨምረው አንዳንድ ኤምባሲ እንዲደበድቡ ይደረግ። ከክረምት በፊት የደርጉን ነገ
ር መጨረስ ያስፈልጋል። ከዚያ የስልጣን ነገር ሽ ያጭሽ አንድ ያገባሽ ነው።

እግዚአብሄር ከረዳን እስከ መስከረም ልጆቹንም አሁን የለመዷትን መደብ ትግል፣ ሰፊው ህዝብ ወዘተ የሚል
ፈሊጥ እናስተዋቸዋለን። የፈላ ጠጅ የደረሰ ልጅ ማስቸገሩ አይቀርምና አባት አንዳንዴም በልጁም ቢሆን መጨከ
ን ይኖርበታል። አንዳንዶቹ ከካብ አይገባ ድንጋይ ናቸውና ከዥብ ለቅሶ የሄደችው አህያ እድል ይገጥማቸዋል።

**ለጥያበሉ ድፋባቸው**

** እዚህ ላይ ሽሙጥ ለዴሞዎች የምትሰጣቸው ማስጠንቀቂያ አለ። እንኳን የሽሙጥን አሰራጮች ሌሎችን ተራማጆች አሁን እንደ ጀመራችሁት ለፖሊስ ብትሰጡ ወይም ብትደበድቡ ሽሙጥ ለፖሊስ ብቻ አትሰጣችሁም። የ36 ዋና ዋና ዴሞዎች ስም እስከነ ህይወት ታሪካቸውና ስራቸው በሚቀጥለው ቁጥሯ ላይ ታወጣለች። እስከዛሬም ያባለጓችሁ የሰፊው ህዝብ ድምፅና የሌሎች ጋዜጦች አዘጋጆች ናቸው።*

-